# ቆሻሻ ማስወገድ እንዲሁም በዑደት መጠቀም

# የመረጃ መመሪያ



# ራእያችን

እንኳን ወደ ዊንዳሃም በደህና መጡ !

ይህ መመሪያ በዊንዳሃም ከተማ የሚቀርቡ የቆሻሻ ማስወገድ አገልግሎቶች በተመለከት አጠቃላይ ምልከታ እና እንዴት ተደራሽ መሆን እንደሚቻል መረጃ የሚያቀርብ ነው። ዊንዳሃም ከተማ ንጹህ እንድትሆን ነዋሪዎችዋ የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ የሚረዳ ነው።

ስለ ሌሎች ቆሻሻ ማስወገድ እና በዑደት መጠቀም አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃና የዚህ መጣጥፍ ትርጉም በተመለከተ የሚከተለውን የድህረ-ገጽ ወይም ከታች ያለው የኪው አር ኮድ ይጠቀሙ።
**www.wyndham.vic.gov.au/services/about-waste-and-recycling**

# ቆሻሻ እንጣል - ቆሻሻን በነጻ እናስወገድ




**ዊንዳሃም ከተማን ንጹህ እናድርጋት**
ቆሻሻ የትም መጣል እና ህገ-ወጥ የቆሻሻ ማስወገድ የዱር እንስሳትን ይጎዳል፤ የውሃ አካላትን ይበክላል፤ እንዲሁም መናፈሻዎቻችንና መንገዶቻችን ያበላሻል። የማይፈለጉ የቤት እቃዎችን እና ቅጠላ-ቅጠሎችን ማስነሳት አገልግሎት ይጠቀሙበት - ቆሻሻ እንጣል

**በካሜራ መቀረጽ**
ዊንዳሃም የከተማ አስተዳደር የከተማ ላይ ቀራጭ ካሜራዎች ተክሏል። በታወቁ የቆሻሻ መጣያ ቦታዎች በየጊዜው በሚያደርገው ክትትል ህገወጥ አሰወጋጆችን ለመያዝ ይሞክራል። የተያዙ አጥፊዎች ደግሞ ይቀጣሉ።

**በነሱ ላይ ጠቁሙ**
አንድ ሰው ቆሻሻ  ሲጥል ካያችሁ፡ ቀኑን፤ ሰዓቱን፤ ቦታውን እና ዝርዝር ጉዳዮችን (ለምሳሌ የመኪናው ታርጋ ወይም መግለጫዎች) እንዲሁም እንደ ፎቶዎች የመሳሰሉትን ማስረጃዎች በመያዝ በሚከተለው ላይ ጠቁሙ።

**www.wyndham.vic.gov.au/raise-request-or-issue**

# የማያስፈልጉ የቤት እቃዎች እና ቅጠላቅጠሎችን መሰብሰቢያ አገልግሎት




**የማይፈለጉ የቤት እቃዎችን እና ቅጠላ-ቅጠሎችን ከቤትዎት ማስነሳት ሶስት ነፃ አገልግሎት**

የዊንዳሃም ከተማ ነዋሪዎች የዑደት መጠቀም ወይም ቆሻሻን እና አላስፈላጊ የቤት እቃዎችን እና ቅጠላ-ቅጠሎችን የማስወገድ የተለያዩ አገልግሎቶች ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

**የማያስፈልጉ የቤት እቃዎችን እና ቅጠላ-ቅጠሎችን ቆሻሻ መሰብሰቢያ አገልግሎት**

አብዛኞዎቹ የዊንዳሃም ነዋሪዎች (ተከራዮችን ጨምሮ) በአንድ የፋይናንስ አመት ሶስቴ የማያስፈልጉ የቤት እቃዎችን እና ቅጠላ-ቅጠሎችን በነጻ ከቤት የማስወገድ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ለመመዝገብ ብቁ ናቸው። ቆሻሻው ከቤት ይወገድ ዘንድ ከሁለት ሳምንት አስቀድመው መመዝገብ ይኖርባቸዋል። የሚወገደው ቆሻሻም ከሶስት ሜትር ኩይብ በላይ መሆን አይኖርበትም (3ሜ X 1 ሜ X 1 ሜ)።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም የማያስፈልጉየቤት እቃዎችን እና ቅጠላ-ቅጠሎችን ማስወገድን በተመለከተ ለመመዝገብ፤ ወደ **1300 023 411** መደወል ይችላሉ። ወይም **www.wyndham.vic.gov.au/services/waste-recycling/hard-and-green-waste-collection-service ይጎብኙ።**

# የቆሻሻ ማስወገድ ቫውቸር | የቫውቸር ለውውጥ



## የቆሻሻ ማስወገድ ቫውቸር - ለቤት ግብር ከፋይ

ዊንዳሃም ከተማ ለቤት ግብር ከፋዮች አንድ ቫውቸር ይሰጣል፤ ይህም አንድ ጭነት ሙሉ ቆሻሻ ወደ ዊንዳሃም ላንድ ፊል እና ሪሶርስ ሴንተር በነጻ እንዲወስዱ ያስችላቸዋል። ቫውቸሩ የሚታተመው በመጀመሪያው የአመታዊ ሬት ኖቲስ (ግብር መክፈያ የአመታዊ ማስታወቂያ) ሲሆን፤ ይህም ቆሻሻ ወደ **470 Wests Rd, Werribee, 3030** በተወሰደ ጊዜ እበሩ ላይ ቫውቸሩን ማሳየት ይገባል።

የቆሻሻ መጠን፣ ገደቦች እና ክልከላዎች አሉ። ለግዴታዎችና ሁኔታዎች ድህረ-ገጹን ይመልከቱ።

## የቆሻሻ ማስወገድ ቫውቸር - ለነዋሪዎች

ብቁ ነዋሪዎች (ተከራዮችን እና ቤታቸው ላይ የሚኖሩትን አጠቃልሎ) ዊንዳሃም ላንድ ፊል እና ሪሶርስ ሴንተር ከአንድ ጊዜ በላይ በነጻ ሊጎበኙት ይችላሉ።

ይህም የሚሆነው ነዋሪዎች  ለመኖሪያ ቤት የተመደበላቸውን የማያስፈልጉ የቤት እቃዎችን እና ቅጠላቅጠሎችን ከቤት የማስወገድ አገልግሎት በቫውቸር ከለወጡት ነው።

በአማራጩ: ነዋሪዎች ቆሻሻ ማስወገጃ ቫውቸር የማያስፈልጉ የቤት እቃዎችን እና ቅጠላ-ቅጠሎች አገልግሎት  ሊለዋወጡት ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ: እባክዎትን ወደ ደንበኞች አገልግሎት የስልክ ቁጥር **1300 023 411** ይደውሉ።

**www.wyndham.vic.gov.au/venues/municipal-tip-refuse-disposal-facility**

## ዊንዳሃም ላንድ ፊል እና ሪሶርስ ሴንተር

ዊንዳሃም ላንድ ፊል እና ሪሶርስ ሴንተር ፡ አድራሻ **470 Wests Rd, Werribee 3030** ከመጎብኘትዎ በፊት የትኞቹ ቁሳቁሶች ወይም ነገሮች በነጻ መወገድ እንደሚችሉ ወይ ክፍያ እንደሚጠይቁ አጣሩ።

### በነጻ ለመጣል (ለብቻ መለየት ይኖርበታል)



### ቆሻሻ የማሰወገድ ቫውቸር በመጠቀም በነጻ ወይም በክፍያ እነዚህ ቁሳቁሶችን ወይም ነገሮችን ማሰወገድ ይቻላል።





የመጠን ገደቦች እና ክልከላዎች አሉ፤ ለዝርዝሩ ድህረ-ገጹን ይመልከቱ።

ስለ ክፍያ፤ ተቀባይነት ስላለው እና ስለሌለው ነገር በተመለከተ
**www.wyndham.vic.gov.au/venues/municipal-tip-refuse-disposal-facility**
ድህረ-ገጽ ይጎብኙ።

# የቆሻሻ ጋን ስለ መሰብሰብ

## የቆሻ ጋን መሰብሰቢያ ቀኔ መቼ ነው?

መቼ ጋን እንደሚሰበሰብ ግር ይላችሁ ይሆን? ከዚህ በታች ቀለል ያሉ ምክሮች ቀርበዋል።

- የዑደት አጠቃቀም ጋን (ብጫ)፡ በየሁለት ሳምንት ይሰበሰባል።
- የቆሻሻ ጋን (ቀይ)፡ በየሳምንቱ ይሰበሰባል።
- ምግብ ነክና የጓሮ ቅጠላ-ቅጠሎች (አረንጓዴ)፡ በየሁለት ሳምንት ይሰበሰባሉ፤ የሚሰበሰበው የዑደት አጠቃቀም ጋን (ብጫ) በማይሰበሰበት ሳምንት ነው።

የቆሻሻ መሰብሰቢያ መርሃ-ግብር በተመለከት የኪው አር ኮዱን ያንሱት ወይም የሚከተለውን የድህረ-ገጽ ይጎብኙ፡
**digital.wyndham.vic.gov.au/mywyndham/**







## ጋኖች እንዴት ማስተዳደር ይቻላል

ጋኖች በትክክል እና በቀላሉ ይሰበሰቡ ዘንድ፤ በዛውም መንገዶች ንጽህናችው ይጠበቅ ዘንድ፡

- በመንገዱ ጠርዝ አጠገብ ጎን ለጎን አስቀምጡዋቸው፤ እጀታችው ከመንገድ ዞሮ (በተቃራኒው) መኖሩን አረጋግጡ።
- በጋኖች መሃከል 50 ሴንቲ ሜትር ቦታ ይተዉ፤ ከዛፎች፤ ከመብራት ይሁን ሌላ ቀዋሚዎች፤ መኪኖች እንዲሁም የመኪና መዞሪያዎች 50 ሴንቲ ሜትር ርቀት ይጠብቁ።
- ጋኖችን ምሽት ከመሰብሰቢያ አንድ ቀን በፊት ውጭ ያውጡአቸው፤ በ24 ሰዓት ውስጥም ወደ ቦታቸው ይመልሱዋቸው።
- ከሚገባ በላይ አይምሉዋቸው፤ መክደኛው መዘጋት አለበት። ከወጭ ተጨማሪ ዘንቢሎች ወይም ሳጠራዎች ካሉ አይሰበሰቡም።

## በሰፊ ግቢ፤ ወይ ብዙ ነዋሪ ባለበት መኖሪያ ህንጻ ለሚኖሩስ?

- ጋኖች ላይ የቤት ቁጥር ይጻፉበት
- በመንገዱ ቀጥተኛ ትዩዩ ቦታ ላይ አኑሩት
- በመሰብሰቢያው ቀናት መኪኖች እንዳይቆሙ አድርጉ።

# በቆሻሻ መሰብሰብ ስራ ላይ እንከን ካለ አሰታውቁ

**የተበላሸ፤ የጠፋ ወይም የተሰረቅ ጋን ካለ አሰታውቁ**

የተበላሹ ጋኖች ሊያፈሱ እንዲሁም ሊያንጠባጥቡ ይችላሉ። ስለነዚሁ ሪፖርት ማድረግ መንገዶቻችን ንጽህናቸው ተጠበቀው እንዲቆዩ ያደርጋል። ስለ ተበላሸ ጋን ሪፖርት ካደረጉ በኋላ፡ ባዶ መሆኑ አረጋግጠው ኔቸር ስትሪፕ ሳሩ ላይ አሰቀምጡ። አብዛኛው ጊዜ ከመሰብሰቢያ ጊዜ ከሁለት ቀናት በኋላ፡ ጋኖች ሊታደሱ ወይ ደግሞ ሊተኩ ይችላሉ።



**የቆሻሻ ጋኔ ካልተነሳሰ?**

ጋንዎት በጊዜ እንዲነሳ፡ ከመሰብሰቢይ አንድ ቀን በፊት ማታ ላይ ውጭ ያኑሩት። ጋንዎ በተባለው ቀን እስከ ከሰዓት 5 ሰዓት ድረሰ ካልተነሳ  ሰለሁኔታው ሪፖርት ያድርጉ። ይህም ጉዳዩን በአግባቡ እንዲስተናገድና መፍትሄ እንዲሰጠው ያግዛል፤ ቆሻሻውን የማንሳቱ አገልግሎት እንዳይቋረጥ ይረዳል።

**የቆሻሻ ጋኖች በአርብ ሰቅለት ቀን፤ በገና እንዲሁም በአዲስ ዓመት አይነሱም። ለነዚህ ቀናት የተያዘው የማንሳት መርሃ-ግብር ወደ ነገታው ይተላለፋል።**

ስላለፈብዎት ቆሻሻ የማንሳት መርሃ-ግብር፤ ስለ ተሰረቁ ወይም ስለተበላሹ ጋኖች ሪፖርት ለማድረግ፤

ኪው እር ኮድ በማንሳት ወይም በሚከተለው ድህረ-ገጽ አማካኝነት አቤቱታዎትን ወይም ጥያቄዎትን ማቅረብ ይችላሉ። **www.wyndham.vic.gov.au/raise-request-or-issue**

በ**1300 023 411** ስልክ ቁጥርም ሊደውሉ ይችላሉ።

# ቆሻሻ (ሰሙናዊ መርሃግብር)

አስታውሱ! እያንዳንዱ በዚህ ጋን ውስጥ የሚቀመጠው ነገር ወደ ጉድፍ ማጠራቀሚያ ሜዳ ነው የሚጣለው። ሜዳው ላይ፡ እንደ ምግብ፤ የጓሮ ቆሻሾች የመሳሰሉት ወደ ግሪንሃውስ ጋዝ ይቀየራሉ። እንደ ፕላስቲክ ወይም ጠርሙዝ የመሳሰሉት ደግሞ አይሰባበሩም።

ስለሆነም፡ በተቻለ መጠን፡ ወደ ጉድፍ ማጠራቀሚያ የሚሄዱትን መቀነስ፤ ዳግም-መጠቀም እና የዑደት አጠቃቀምን መተግበር ያስፈልጋል።

- ምግብና የጓሮ አትክልት ነክ ቆሻሻ በአረንጓዴው ጋን አኑሩት፤ ወይም ደግሞ ለማዳበሪያ ይጠቀሙበት።
- የዑደት አጠቃቀም ተግብሩ
- ኢ-ቆሻሻዎችን ለመጣል የከተማ ምክር ቤት መጣያ ቦታ ውሰዱት ወይም ከማያስፈልጉ የቤት እቃዎችን እና ቅጠላቅጠሎች ጋር አኑሩዋቸው።
- የማስወገጃ አማራጮችን በኦን ላይን A-Z የቆሻሻ መመሪያ ታገኙታላችሁ።


የተሰባበሩ ብርጭቆ ነኮች እንዲሁም ማንኪያና ሹካ ነኮች


ተገልግላችሁ የምትጥልዋቸው ኩባያዎች


ያረጁ ልብሶች፤ ጫማዎች እንዲሁም አልባሳት


የህጻናት ናፒ



የላስቲክ ከረጢቶች፤ ለስላሳ የፕላስቲክ መጠቅለያዎች እንዲሁም የምግብ መጠቅለያዎች


በከረጢት የሚያዙ ማናቸውም ነገሮች የተዝረከረኩ ቆሻሾች


የድመት ወይም የእንስሳ አይነ-ምድር





በከረጢት ላይ ያለ ፓሊስትሬን ወይም የተነፋ ፍራሽ መሳይ


የወረቀት ፎጣ ወይም የወረቀት ማበሻ



ረዢም ጊዜ የሚቆይ ወተት መያዣ ካርቶን ወይም ቴትራ ፓክስ

**አይደለም**



ባትሪ ፣ የሚቀጣጠሉ ፈሳሾች እና አደገኛ ቆሻሾች እንዳይኖሩ

# በዑደት መጠቀም (በየሁለት ሳምንት)

በዑደት በትክክል መጠቀም የሚያስገኘው ጥቅም ለዑደት የመረጥናቸው በትክክል ዳግም ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ከጉድፍ ማጠራቀሚያ እነዚህን ማስቀረት ማለት በዛው ተፈጥሮ ሃብትን ጠበቅን ማለት ነው፡፡

## በዑደት መጠቀምን ትክክለኛ እንዲሆን ምን ማድረግ ይቻላል

- ✓ መያዣዎች እንደ ጣሳዎች እንዲሁም ጠርሙሶች ባዶአቸው መሆን አለባቸው፡፡ ምግብ፤ ፈሳሽ ወይም ሌላ ነገር እንዳይዙ ማድረግ፡፡
- ✓ መክደኛ እንዲኖር ማድረግ፡፡
- ✓ ጠንካራ የፕላስቲክ መያዣዎች እንዲሁም ጠርሙሶች ማለትም እንደ የወተት ጠርሙሶች፤ የሻምፓ ጠርሙሶች እንዲሁም የፕላስትክ ጊዜያዊ መያዣዎች ብቻ፡፡
- ✗ ለስለስ ያሉ ፕላስቲኮች ከሆኑ፤ እንደ ምግብ መጠቅለያ የቺፕስ መያዣ ላስቲኮች ወይም የላስቲክ ከረጢቶች ከሆኑ ሁሉም ወደ ቀዩ ጋን ይገባሉ፡፡



**ወረቀት እና ካርቶን መሳዮች**
ጋዜጣ፤ የቢሮ እና ማተሚያ ወረቀቶች፤ መጸህፍት፤ መጽሄት እንዲሁም ካርቶኖች



**አልሙኒየም እና ብረት**
ባዶ ኤሮሶል፤ ፎርቆር፤ ጣሳ፤ መጠቅለያዎችና(ፎይል) እና የሳህን መጠቅለያዎች



**ባዶ የብርጭቆ ጠርሙሶች**
እና የጠርሙስ መያዣ፤ ከነመክደኛው እንዲሁም ጠቋሚ የተለጠፉ ጽሁፎች ያሉበት




**• ሁሉም ነገር ወደ ዑደት እንዲሰበሰብ በካርቶን ወይም በመያዣ መሆን የለበትም፡፡**

**• በዚህ ረገድ ጥንቃቄ ይደረግ፡ ወደ ሌሎች የዑደት መጠቀም ጋኖች ሌሎች ቆሻሾች እንዳይገለበጡ አባክዎትን ይጠንቀቁ፡፡**



**ጠንካራ የላሲትክ መያዣዎች እና ጠርሙሶች**
ከማድቤት፤ ከልብስ አጥበት እንዲሁም ከገላ መታጠቢያ፡፡ ከፕላስቲክ ኮዶች 1፤ 2፤ እና 5 ጋር ብቻ፡፡






ከረጢት እንዳይኖር ወይም በከረጢት የተቀመጡ ዕቃዎች እንዳይኖሩ፡፡

**አይደለም**




ባትሪ ፣ የሚቀጣጠሉ ፈሳሾች እና አደገኛ ቆሻሾች እንዳይኖሩ

## ምግብና የጓሮ አትክልት ልቅምቃሚዎች (በየሁለት ሳምንት)

ምግብ እና የጓሮ አትክልት ቅጠላ-ቅጠሎች አረንጓዴ ጋን ውስጥ ከተጣለ ወደ አትክልት ማዳበሪያ ይቀየራል። ማዳበሪያውም ፓርክ፣ አትክልት እና እርሻ ልማት ላይ ይውላል።



አሳ፤ ስጋ እንዲሁም አጥንቶች



የፍራፍሬ እና የአትክልት ልጣጮች



ወተት እና የወተት ውጤቶች እንዲሁም እንቁላል



ዳቦ፤ ፓስታ፤ ሩዝ እንዲሁም የምግብ እህሎች



ሻሂ ቅጠል (ያልታሸገ)፤ ቡና



ትራፊ ምግብ



ከጓሮ አትክልት የወዳደቀ፤ ከግቢ ሳር ከክርክም የወደቀ፤ አነስተኛ ቅርንጫፎች፤ ቅጠሎችና አረሞች






### Get a free kitchen caddy (ትንሽዬ የኩችና ቆሻሻ ማጠራቀሚያ)

እቤት ውስጥ የምግብና የጓሮ አትክሎቶች ውድቅዳቂ ማጠራቀሚያ ጋን ካልዎት፤ ትንሽዬ የኩችና ቆሻሻ ማጠራቀሚያን ማግኘት ትችላላችሁ። በነጻ ትንሽዬ የኩችና የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ከአንዱ መሰብሰቢያ ማእከል መውሰድ ይችላሉ።

ስለ የምግብና የጓሮ አትክሎቶች ውድቅዳቂ ማጠራቀሚያ ጋን እንዲሁም ትንሽዬ የኩችና ማጠራቀሚያ ለማወቅ ለበለጥ መረጃ የሚከተለውን ይጎብኙ: **www.wyndham.vic.gov.au/services/waste-recycling/household-bins/household-bin-services**

አይደለም




ባትሪ ፣ የሚቀጣጠሉ ፈሳሾች እና አደገኛ ቆሻሾች እንዳይኖሩ

# ማዳበሪያ ጋኖች እንዲሁም ኣታክልት ትል እርሻዎች



### ማዳበሪያ ጋኖች እንዲሁም ኣታክልት ትል እርሻዎች የድጎማ መርሃ-ግብር

ዊንዳሃም ነዋሪዎች ኣታክልት ትል እርሻ ወይም ማዳበሪያ  ምርት ለሚጠቀሙ እስከ 50 በመቶ ቅናሽ ይሰጣል። ይህም የሚሆነው በየፋይናንስ አመቱ ከዎርምላቨርስ (Wormlovers) ድርጅት ነው።

ስለ ማዳበሪያ ወይም ምርቶችን ስለማዘዝ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፤ የሚከተለዉን ድረ-ገጽ ይጎብኙ። **www.wyndham.wormlovers.com.au**

### ለምን ማዳበሪያ ያስፈልጋል?

ኣታክልት ትል እርሻዎች እንዲሁም ማዳበሪያ ጋኖች ወደ ጉድፍ ማጠራቀሚያ የሚላከውን ኦርጋኒክ ቆሻሻ ለመቀነስ ቀላል ዘዴ ናቸው። በተጨማሪ የምግብ ትራፊዎችና ልጣጮች በአልሚነት ወደ በለጸጉ ማዳበሪያዎች እንዲቀየሩ የሚያደርግ ዘዴ ነው።

# ኢ-ቆሻሻና አደገኛ ቆሻሻ




**ባትሪና የኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ** (ኢ-ቆሻሻ)

ኢ-ቆሻሻ ወይም የኤልክትሮኒክ ቆሻሻ ማናቸውም የማይፈለግ ወይም የተሰበረ ዕቃ ሆኖ፤ ባትሪ ወይም የኤልክትሪክ[NS2.1] ገመድ ያለው ማለት ነው።

በኩርባ በሚቀመጥ የቆሻሻ ጋን ውስጥ እንዲሁም በጉድፍ ማጠራቀሚያ ኢ-ቆሻሻን መጣል በቪክቶሪያ ህገ-ወጥ ተግባር ነው። በጉድፍ ማጠራቀሚያ ውስጥ እሳት ሊያቀጣጥል ይችላል፤ እንዲሁም አደገኛ ኬሚካሎች ወደ አየር፤ አፈር እንዲሁም ውኃ ሊቀላቀሉ ይችላሉ።

እንደ ባትሪ፤ የተንቀሳቃሽ ስልክ ቆፎ እንዲሁም መለዋወጫዎች የመሳሰሉት አንስተኛ ኢ-ቆሻሾች ወደ ዊንዳሃም የዑደት ጣብያዎች ወይም ወደ ኢ-ቆሻሻ መሰብሰቢያ ጣብያዎች በመውሰድ የዑደት ስራ መስራት ይቻላል። ትላልቅ ኢ-ቆሻሾች ወደ ዊንዳሃም ላንድ ፊል እና ሪሶርስ ሴንተር በነጻ መውሰድ ይቻላል ወይም ደግሞ ከማያስፈልጉ የቤት እቃዎችን እና ቅጠላ-ቅጠሎች መሰብሰቢያ ዘዴ ቀጠሮ በማስያዝ ሊሰበሰብ ይቻላል። ስለ ኢ-ቆሻሻ እንዲሁም ማስወገጃ መንገዶቹ ለበለጠ መረጃ ኪው አር ኮዱን ያንሱት፤ ወይም ደግሞ የሚከተለዉን የድህረ-ገጽ ይጎብኙ።

**www.wyndham.vic.gov.au/ewaste**

- ባትሪዎች
- ቀላል ኣምፑሎች እንዲሁም የፍሎረሰንት ቱቦዎች
- ተንቀሳቃሽ ስልኮች
- ኮምፒውተሮች እንዲሁም መለዋወጫዎች
- ቴሌቪዥኖች እና ሬድዮኖች
- በባትሪ የሚሰሩ አሻንጉሊቶች
- የጆሮ ማዳመጫዎች
- ንፋስ አምጪ እቃዎች
- ገመዶች
- ፍሪጅ፣ ማይክሮዌቭ፣ የልብስ ማጠቢያ ዕቃዎች
- የኩችና ዕቃዎች
- የኤልክትሪክ መሳርያዎች




**የሚቀጣጠሉ ፈሳሾች፤ አደገኛ ኬሚካሎች ወይም በካይ ቆሻሻ**

ኬሚካል እንዲሁም በካይ ቆሻሻ እንደነ ቤንዚን፤ ማቅጠኛ፤ አሴቶን እንዲሁም አስቤስቶስ በመንገድ ዳር ላይ ወይም በወራቢ ጉድፍ ማጠራቀሚያ አይጣሉም (አይቀመጡም)። ስለ ማስወገድ መረጃ ለማግኘት ከ A-Z የሚለውን የቆሻሻ ማስወገድ መመሪያ ይመልከቱ።

**www.wyndham.vic.gov.au/waste-guide**

# ሌሎች የዑደታዊ አጠቃቀም አማራጮች




### የኮምዩኒቲ ዑደታዊ አጠቃቀም ጣብያዎች

ዑደታዊ አጠቃቀም ጣብያዎች በተለያዩ ኮምዩኒቲ ሴንተር ውስጥ ይገኛሉ። ዝርዝራቸውም እንደሚከተለው ነው

- በእጅ የሚያዙ ባትሪዎች
- የማተሚያ ካርትሪጆች
- ሲዲዎች እና ዲቪዲዎች
- አነስተኛ የመብራት አምፑሎች እና ቱቦዎች
- ተንቀሳቃሽ የስልክ ቀፎች እንዲሁም መለዋወጫዎች
- ኤክስ ሬይ (ራጂ)




### አልባሳት እንዲሁም ኢ-ቆሻሻ መጣያ ማእከላት

የኤሌክትሪክ ቆሻሻ (ኢ-ቆሻሻ) እንዲሁም አልባሳት በተለያዩ ዘዴዎች ዳግም ጥቅም ላይ ሊውሉ እንዲሁም በዑደት አጠቃቀም ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ ይቻላል። ይህም ሲባል መንገድ ዳር በሚቀመጥ ጋን ማለታችን አይደለም። የኢ-ቆሻሻ እና የአልባሳት መጣያ ማዕከላት በዊንዳሃም ዙርያ በብዙ ኮምዩኒቲ ሴንተር አካባቢ በመኪና ማቆሚያ አካባቢዎች ይገኛሉ። አድራሻቸውን ለይቶ ለማወቅ ድህረ-ገጹን ይመልከቱ፡

See: **www.wyndham.vic.gov.au/services/waste-recycling/other-waste-recycling-services**

## የማጠራቀሚያ መያዣ ስርዓት




**Victorian Container Deposit Scheme (ኮንቴይነር ዲፖዚት ስኪም)**

ዊንዳሃም እንደ ጣሳ እና ጠርሙስ የመሳሰሉ ብቃት ያላቸው ማጠራቀሚያዎች የምትወረውርበት በርካታ ስፍራዎች አሉት፤ በዛውም የ10 ሳንቲም ክፍያ ያገኛሉ።

ስለ ብቃት ያላቸው ማጠራቀሚያዎች ተጨማሪ መረጃዎች ለማግኘት የሚከተለውን የድህረ-ገጽ ይመልከቱ፡ **mytomra.com.au/locations/vic-container-deposit-scheme/**

## ቆሻሻን ይቀንሱ

ቆሻሻ እንዳይኖር ለማድረግ የመጀመሪያው ተመራጭ መንገድ ቆሻሻው ራሱ እንዳይፈጠር ማድረግ ነው።

በአነስተኛ መጠን ስትገዙ እንዲሁም በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ነገሮችን ስትገዙ፤ የሚጣል ነገር ይቀንሳል። ይህ ደግሞ በተራው በኣካባቢ ላይ የሚኖረውን ጉዳት እንዲቀንስ ያደርጋል።

እነዚህን ቀላል የዕለት ተዕለት ተግባራት በመሞከር ቆሻሻን ይቀንሱ።

- ዳግም ጥቅም ላይ የሚውሉ ከረጢቶች፤ ኩባያዎች እንዲሁም ጠርሙሶች
- አዲስ ከሚገዙ ይልቅ ያገለገለ ይግዙ
- የሚያስፈልግዎትን ብቻ ይግዙ!
- ጥሩ ጥራት ያላችው ሆኖም የማይፈለጉ ዕቃዎች/ቁሳቁሶች ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ለእርዳታ ለግሰዋቸው። ብዙ መጠቅለያ ያላቸውን ምርቶች አትግዟቸው/አሰወግዱዋቸው።
- የምግብ ትርፍራፊን ለማዳበሪያ ጋኖች እንዲሁም ኣታክልት ትል እርሻዎች ይጠቀሟአቸው።
- በአካባቢ የጽዳት በዓላት ላይ ይሳተፉ።
- የራስዎን አታክልት እና እና ቅጠላ ቅጠል ያሳድጉ።
- በድጋሚ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ናፒ ጨርቆች እና የንጽህና እቃዎች ይጠቀሙ።

ስለ ቆሻሻ መቀነስ እና ጥሩ ጥራት ያላቸውን ቁሳቁሶች እንዴት እንደምትለግሱ የሚለውን አካቶ ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለዉን የድህረ-ገጽ ይጎብኙ፡ **www.wyndham.vic.gov.au/reduce-waste**

**እያንዳንዱ ትንሽ እርምጃ ተደምሮ ትልቅ ልዩነት ያመጣል!**
የዊንዳሃም ግሪን ሊቪንግ ተከታታይ ሲሪስ፡ አውደ ጥናት
(Wyndham's Green Living Series: Events & Workshops)

ዊንዳሃም የከተማ ምክር ቤት አመቱን ሙሉ ቆሻሻን የሚቀንሱበት፣ በተሻለ መንገድ ዑደት የሚያካሂዱበት፤ ጥቅም ላይ የሚውሉ ጥበቦች፤ እንዲሁም ስለ ገንዘብ ቁጠባ ውይይት የሚደረግባቸው ነጻ አውደ-ጥናት ያዘጋጃል።

በቅርቡ ለሚኖረው አውደ ጥናት ይከታተሉ !
**www.wyndham.vic.gov.au/greenlivingseries**



# መስተጋብር ያለው የነዋሪ አካባቢ ቆሻሻ መጣል መመሪያ



## የሚጣል ግን የት እንደሚጣል እርግጠኛ ያልሆኑበት ቆሻሻ አልዎት?

መስተጋብር ላይ የተመሰረተው A-Z የቆሻሻና የዑደት አጠቃቀም መመሪያ ተከታተሉት። ድህረ-ገጽ በመጎብኘት ሊያሰወግዱ የፈለጉት ቁሳቁስ ወይም ዕቃ ለይተው ይፈልጉ። ይህም ያሉትን የማሰወገጃ ዘዴዎችን እንዲያዉቁ ይረዳዎታል።

ለተጨማሪ መረጃና ለቁሳቁሶችና ዕቃዎች ዝርዝር፤ እባክዎትን የሚከተለዉን ይመልከቱ። **www.wyndham.vic.gov.au/waste-guide**

እንዱን ቁሳቁሰ ዝርዝር ውሰጥ ካላገኙት፤ ወይም ተጨማሪ መረጃ ካሰፈለግዎት፤ እባክዎትን በ **wastewise@wyndham.vic.gov.au**
**1300 023 411** የምክር ቤት የቆሻሻ ትምህርት ቡድንን ያናግሩ

Interpreter

ለጽሁፍና ቃል ትርጉም አገልግሎት በ 131 450 ስልክ ይደውሉ።

ਪੰਜਾਬ (Punjabi)

हिंदी (Hindi)

普通话 (Mandarin)

العربية (Arabic)

Tiếng Việt (Vietnamese)

ကညီကျိာ် (Karen)

## ያግኙን


ድህረ ገጽ፡
**www.wyndham.vic.gov.au**

ኢሜይል
**mail@wyndham.vic.gov.au**

ስልክ፡
**1300 023 411**



ይህ ወረቀት መቶ በመቶ በዑደት ጥቅም ላይ በዋለና ከክሎሪን ነጻ ቀለምን በመጠቀም ታትሟል።


wyndhamcity
city.coast.country